# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 84 ታህሳስ 15 2002 ዓ.ም

## ግንቦት 7 የወያኔው የይስሙላ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ንቅናቄውን ይበልጥ ለትግል ያነሳሳዋል ሲል መግለጫ አወጣ

ንቅናቄው ባወጣው መግለጫ የይስሙላው ፍርድቤት በ5 የነጻነት ታጋዮች ላይ ሞት፣ በ33ቱ ላይ ደግሞ የእድሜልክ እስራት መወሰኑ፣ አገዛዙ የገባበትን የዝቅጠት ደረጃ ያሳያል ብሎአል። ወያኔ እንደልቡ በሚቆጣጠረው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ፣ አገዛዙ ከታሪክ አለመማሩን ያሳያል ያለው ግንቦት 7፣ ለነጻነት የሚደረገው ትግል በሞትና በእድሜልክ እስራት ፍልድ ጋጋታ ለአፍታም እንደማይስተጓጉል ገልጿል። የኢትዮጵያ ህዝብም የተለያዩ እርምጃዎችንም እንዲወስድ ጥሪ አስተላልፎአል። የመግለጫውን ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ይነበባል

## ለነጻነታችንና ለተዋረደው ስብዕናችን መከበር ስንል ልንከፍለው የማንፈልገው መስዋዕትነት እንደሌለ ወያኔን የማሳወቂያ ጊዜው አሁን ነው

ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ

በጉልበት በተገኘ ስልጣን የአገሪቱን አንጡራ ሃብት በመዝረፍ የከበረው የወያኔ ቡድን በእብሪት ተወጥሮ ተቃዋሚዎችን “መንገዱን ጨርቅ ያድረግላችሁ” ሲል እንዳልነበረ፤ የአገራቸው በዘረኞችና በአምባገነኖች መዳፍ ስር መውደቅ አንገብግቦአቸው ገና ለትግል ከመሰባሰባቸው በድንጋጤ ድባብ ውስጥ ተዘፍቆ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን እንዳሳጣው ከአንተ ከጉዳዩ ባለቤት በላይ ምስክር ሊሆን የሚችል ሌላ ሀይል የለም። ወያኔን ተስፋ እንዲቆርጥ ያደረገው አንተ የኢትዮጵያ በየጊዜው የምታሳየው ጥንካሬ ነው፤ እየደረሰብህ ባለው እስራትና እንግልት ሳትንበረከክ፤ ወያኔ አንተኑ አፍኖ ለመግዛት ሆን ብሎ በፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ ሳትበገር ወያኔን በህቡና በይፋ ለመታገል መወሰንህ ወያኔን እንቅልፍ አሳጥተህ እንዲደናበር ማድረግህ ማንም የሚስተው አይደለም። የወያኔ መደናበር ከልክ ማለፉን ለመረዳት ሰሞኑን በግንቦት 7 አባላትና ለአገራችው ነጻነት በመቆርቆር ድምጻቸውን በማሰማታቸው የሞትና የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸውን ወታደራዊ መኮንኖች፣ ወ/ት ብረቱካንንና ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እሰረኞችን መጥቀሱ በቂ ነው።

የወያኔው የይስሙላ ፍርድ ቤት በ5 ኢትዮጵያውያን ላይ ሞት፣ በ33ቱ ላይ ደግሞ የእድሜልክ እስራት ውሳኔ ማስተላለፉን ሰምተሀል (ሻል)። በውኑ እንዲህ አይነት ፍርድ የሚገባቸው እነማን ነበሩ? ገና ህይወትን ሳያጣጥሙ፣ ለአገራቸውና ለህዝባቸው የሚጠቅም ስራ ሰርተው ለማለፍ ሲያልሙ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች በአጋዚ ጥይት የጨፈጨፈው የአውሬው የመለስና የበረከት ቡድን፣ ወይስ ልጆች በነጻነት እንዲማሩና አገራቸውንም እንዲጠቅሙ የነጻነትን ትምህርት ያስተማሩዋቸው የኢትዮጵያ ታጋይ ልጆች? በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በሶማሊያ፣ በኦጋዴን፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በቤንሻንጉል ወዘተ “ኢትዮጵያውያን ተራብን ተጠማን፣ አስተዳደራዊ በደል ደረሰብን፣ እንደ ሶስተኛ ዜጋ እየኖርን ነው፣ በአገራችን የመማር፣ የመስራት መብታችን ይከበርልን፣ በፈለግነው መሪ እንተዳደር” ብለው የጠየቁትን ኢትዮጵያውያንን እንደ ፋሲካ በግ እያረደ በየመንገዱ የጣላቸውን የአውሬዎች ስብስብ ወይስ፣ ለዜጎች እኩልነትና ብልጽግና የሚታገሉት የኢትዮጵያ ልጆች? አገራችን መሬቷ ተቆርሶ ለባእድ አገር እንዲሰጥ፤ ደሀው ገበሬ የሚያርሰው መሬት ባጣበት ሰአት ለግል ሀብት ማካበቻ ሲባል ገበሬውን እትብቱ ከተቀበረበት ቦታ እያፈናቀለ ለቻይና፣ ለህንድና ለአረብ ነጋዴዎች የሚቸበችበው፤ በአገራችን ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የአንድን ብሄር አገዛዝ በመላው አገሪቱ ያሰፈነው የወያኔው የሽፍታ ስብስብ ወይስ ዲሞክራሲ የሰፈነባት፣ ሰብአዊ መብቶች የተከበሩባትና የህግ ልእልና የሰፈነባትን አገርን ለመመስረት የሚታገሉት ኢትዮጵያውያን? ወያኔ ልብ ካለው፣ ልብ ብሎ እንዲሰማ የምንፈልገው፣ የግንቦት 7 አባላት የወያኔው የይስሙላ ፍርድቤት በሰጠው ፍርደ ገምድል ውሳኔ ይበልጥ ለትግል የነሳሳሉ እንጅ ቅንጣት ታክልም ከአላማቸው የማይዘናጉ መሆናቸውን ነው። ውሳኔው አገራችን በቶሎ ነጻ ካልወጣች ከዚህ የበለጠ ጉዳት ሊደርስባት ይችላል ብለው እንዲጨነቁና ትግላቸውን እንዲያፋጥኑ ያደርጋቸዋል እንጅ፣ “ሞት ከተፈረደብንማ አንታገልም” ብለው እጃቸውን አጣጥፈው እንዲቀመጡ አያደርጋቸውም።

ግንቦት 7 ለነጻነታቸው ሲሉ ለመሞት የቆረጡ ኢትዮጵያውያንን ያሰባሰበ፣ አንድ ሞት አይደለም አንድ ሺ ሞት ቢመጣ ሁሉንም እንደ አመጣጡ ለማስተናገድ ውሳኔ አድርገው የሚታገሉ ኢትዮጵያን ያሰባሰበ ንቅናቄ ነው። ይህንን ደግመን ደጋግመን ለወያኔ መንገር እንፈልጋለን።

### ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ፣

ወያኔ የይስሙላ ፍርዱን ሲያስተላልፍ “ለሌሎችም መቀጣጫ ይሆናል” ብሎ መናገሩን ሰምተሀል። ይህ በቀጥታ ለአንተ የተላለፈ መልእክት ነው። መልእክቱ ስለነጻነትህ እንዳትጠይቅ፣ ኑሮ ተወደደብኝ ብለህ እንዳታማርር፣ ፍትህ ጎደለብን ብለህ እንዳታጉረመርም በአጠቃላይ በአገርህ ላይ ባለቤትነት እንዳይሰማህ፣ በአገርህ ላይ የመወሰን መብት እንዳይኖርህ ለማድረግ የተላለፈ መልክት ሲሆን፣ ይህን ካላደረክም ሞትና የእድሜ ልክ እስራት (**ወደ ገጥጽ 2 ዞሯል**)

## ግዜ

## ወያኔን ከነተከለብን ዘረኝነት ማስወገድ ከችግሮቻችን ሁሉ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር በመሆኑ በኅብረት እንነሳ!!!

መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ውስጣዊ ጭንቀቱን በጋዜጣዊ መግለጫዎች ለማሻር ብዙ ለፍቷል። በእነዚህ ቃለምልልሶች “አልሰማሁም”፣ “አላነበብኩም” ባላቸው በርካታ ጉዳዮች ላይ ሳይቀር ዘላብዷል። ከሁሉም የሚብሰው ግን በጄኔቫ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ የአሜሪካ አምባሳደር የሆኑት ሚስተር ዳግላስ ግሪፍትስ በሰጡት አስተያየት ላይ የሰጠው አሳፋሪ ምላሽ ነው። በተባበሩት መንግሥታት የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ በተገመገመበት ወቅት አሜሪካዊው አምባሳደር ዳግላስ ግሪፍትስ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣኖች በአንድ ዘውግ አባላት መያዛቸውና ይህም ለሃገሪቱ የማይበጅ መሆኑን አስተያየት ሰጥተው ነበር። መለስ ለዚህ ቅን አስተያየት የሰጠው ምላሽ “እኔ እንዲህ ዓይነቱን ድድብና አልሰማሁም። በእውነት ተብሎ ከሆነ አባባሉ ጄኔቫ ያለውን ሰውዬ ደደብነት ነው የሚያረጋግጠው” የሚል ነበር።

መለስ ለምን ወደተራ ስድብ ወረደ? ለምን ከስድቡ በፊት የአምባሳደሩን አስተያየት በማስረጃ አልሞገተም? በእኛ እምነት ምክንያቱ አንድ ብቻ ነው። መለስ ዲፕሎማቶችን ሲያጭበረብርበት የነበረው ጭንብል በከፊልም ቢሆን መገፈፉ ዱብ እዳ ሆኖበታል። እናም ይህንን መርዶ ላመጣለት ንግግር ምላሹ ቁጣና ስድብ ሆነ።

የአምባሳደሩ አነጋገር ለእውነት የተጠጋ ቢሆንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው ማለት ግን አይደለም። እውነታው አምባሳደሩ ካሉት በእጅጉ የጎላ ነው። ሃቁ የወያኔ ከፍተኛ የሥልጣን እርከኖች ከአንድ ብሄር በፈለቀ የሽፍታ ቡድን መያዛቸው ነው። ለማስረጃም ያህል ከዚህ በፊት በወያኔ ጦር ሠራዊት ውስጥ ካሉት 61 ቁልፍ የሃላፊነት ቦታዎች 57ቱ በትግራይ ተወላጅና ነባር የወያኔ አባላት ስለመያዛቸው የስም ዝርዝራቸውን በማውጣት ማጋለጣችን ይታወቃል። ኦሮሞው፣ አማራው፣ ሶማሌው፣ አፋሩ፣ ሲዳማው፣ ወላይታው፣ ጉራጌው፣ አኝዋኩ፣ ጋምቤላው በአጠቃላይ ከትግራይ በስተቀር ሌላው ኢትዮጵያዊ ከጦር ሠራዊቱ ወሳኝ የኃላፊነት ቦታ ሙሉ በሙሉ መገለል ጤነኛ አደረጃጀት ነው እንዲባል ነው መለስ የሚፈልገው? ይህ አደረጃጀት ለዘረኝነት መዋቅራዊ መሠረት መስጠት አይደለምን?

መዋቅራዊ ዘረኝነት የሰፈነው በጦር ሠራዊቱ ውስጥ ብቻ አይደለም። በኢኮኖሚውም ዘርፍ **የኤፈርት አስራ አምስት፣ የደጀና ኢንዶውመንት ሰባት** እንዲሁም **በአክሲዮን ሽፋን የተቋቋሙ ሠላሳ በድምሩ አምሳ ሁለት** ግዙፍ የወያኔ **ኩባንያዎች** ሁሉን የኢኮኖሚ ዘርፍ ተቆጣጥረው ነፃውና ለፍቶ አዳሪውን ኢትዮጵያዊ ከገበያ ውጭ እያደረጉት መሆኑን አሳውቀናል። እነዚህ ድርጅቶች በሙሉ ወያኔ በዘረፋ ለዘረፋ ያቋቋማቸውና ሁሉም የሚመሩት የወያኔ አባላት በሆኑ የትግራይ ተወላጆች መሆኑ **እውነት** ነው።

ከመንግሥታትና ከዓለም ዓቀፍ በጎ አድራጊ ድርጅቶች የሚመጣውን የእርዳታ ገንዘብ ለመቀበልም ያመች ዘንድ ገለልተኛ የሆኑ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የሚያሽመደምድ ህግ በማውጣትና ሜዳውም ለትግራይ ልማት ማኅበርና መሰሎቹ እንዲለቀቅ መደረጉን ዛሬ ለጋሽ አገሮችም የተገነዘቡበት ወቅት ላይ ነን። ይህ ሁሉ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን ለውጭ አገር ታዛቢዎችም ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ የመለስ የማጭበርበርያ ጭንብል እየወለቀ ነው።

ለመለስ የቀረው ማስመሰያ የሲቪል አስተዳደሩ ብቻ ነበር። የአምባሳደር ዳግላስ ግሪፍትስ አስተያየት መለስን ያስገነዘበው እሱም እየተገፈፈ መሆኑን ነው። እናም “**ደደብ**” የሚለው ቃል የመጣው በእፍረትና ንዴት ከበገነ አእምሮ መሆኑን መገመት ይቻላል።

የወያኔ የሲቪል አስተዳደር ለይስሙላ ያህል የሌላ ዘውግ አባላት በሚኒስትርነት፣ ምክትል ሚኒስትርነት እና ሚኒስትር ዴኤታነት የተመደቡበት ቢሆንም በሌላ አገር አቻ ምሳሌ በማይገኝለት ሁኔታ የመምሪያ ኃላፊ የሆነው ወያኔ ሚኒስትር የሆነውን ምስለኔ የሚቆጣጠርበት ሥርዓት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሚኒስትሮች በመለስ አማካሪነት ስም ለተቀመጡ አውራ ወያኔዎች ተጠሪ የሆኑበት፤ በዚህም ምክንያት ከትግራይ ዘውግ ውጭ የመጡ ሚኒስትሮች ከታችም ከላይም በወያኔ የዘወትር ቁጥጥር ስር ያሉ ባሮች የሆኑበት ሥርዓት ነው። እውነተኛውን ሥልጣን የያዙት የመለስ አማካሪዎች የሚኒስትርነት ማዕረግ ስላላቸው በሚኒስትሮች ም/ቤት መለስ የአለቃ አለቃ ሲሆን፤ ሚኒስትሮቹ ደግሞ የምንዝር ምንዝሮች ይሆናሉ ማለት ነው። በወያኔ የሲቪል አስተዳደር እውነተኛ ሥልጣን ያለው በመለስ ዜናዊ፣ አባይ ፀሃዬ፣ ንዋይ ገብረአብ፣ ስዩም መስፍን እና በረከት ስምኦን መዳፍ ውስጥ ሲሆን ሌሎቹ “የተከበሩ ሚኒስትሮች” ከአጫፋሪነት ያለፈ ሚና የላቸውም። (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## በባርነት አገር የሚኖሩ ነፃ ሰዎች

የተፈጥሮ መብቶቻችን ሰው የመሆናችን ፀጋዎች ናቸው። ወያኔን የምንታገለው ነፃነታችንን እንዲሰጠን አይደለም። ትግላችን በተፈጥሮ የተሰጡን መብቶች እንዲከበሩ ነው። ነፃነታችን ዘላለማዊ፣ ከወያኔ እድሜ ቀድሞ የኖረና ከወያኔ ሞት በኋላም የሚኖር ነው። ሆኖም ግን ነፃነታችንን ማስከበር ካልቻልን ከሰውነት ደረጃ ወርደን ባርነትን መቀበል አይቀሬ ነው።

ነፃ ሰው ነፃነቱን የሚያከብርለት ሥርዓተ ህጎችን በማክበር ለማህበረሰቡ ያለውን ግዴታ ይወጣል። ነፃ ሰው ነፃነቱን የሚያከብርለትን ሥርዓት ይንከባከባል። በአንፃሩ ደግሞ ነፃነቱን የማያከብርለት ሥርዓትን ይታገላል፤ ታግሎም ይለውጠዋል።

ከወራት በፊት የወያኔን መንግሥት ሊገለብጡ ሲሉ ተያዙ ተብለው የመለስ ዜናዊ አሻንጉሊት አቃቤ ህጎች እና ዳኞች ወደሚያላግጡበት ፍርድ ቤት የተወሰዱት ወደ አርባ የሚጠጉት ዜጎች ነፃ ሰዎች ናቸው። የራሳቸውንና የአገራቸውን ነፃነት ለማፈን የቆመን ኃይል በመታገል ለራሳቸውና ሕዝባቸው ነፃነት ቀናዒነታቸው በተግባር አስመስክረዋል፤ አርዓያነታቸውን እንከተላለን። ነፃነት ከውጤት ጋር ብዙም አይገናኝም፤ ውጫዊ ነገርም አይደለም። ነፃነት ውስጣዊ ነው – ነፃነት ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር ከብዙዎቻቸን ይበልጥ ጀኔራል ተፈራ ማሞ፤ ጓደኞቻቸው እና ወይዘሪት ብርትኳን ሚደቅሳ ነፃ ሰዎች ናቸው። ለየራሳቸው ህሊና ታማኝ ሆነው ተገኝተዋልና! የሰው ነፃነት በማይከበርበት እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሃገር፣ የነፃ ሰው ኑሮው ወይ እስር ቤት አልያም ጦር ሜዳ ነው። ለነፃነት መታሰር፣ መታገል እና መሞት ከምቾች ባርነት በብዙ እጥፍ የበለጠ የነፃነት ስሜትን ይሰጣል።

ባርነት በገመድ ታስሮ ከቤት መወሰድ እና በገበያ መሸጥ ብቻ የሚመስላቸው ይኖራሉ። ወያኔ ግፍን ደጃፋቸው ላይ እየፈጸመ፣ ሥራውም ኢ-ፍትሃዊ መሆኑን እያመኑ "እኔን አልነኩኝ" እያሉ በዝምታ መኖር በነፃነት የወሰኑት የጥበብ እርምጃ የሚመስላቸው አሉ። ኢ-ፍትሃዊውን አገዛዝ በፈቃዳቸው ከሚያገለግሉትም ውስጥ አንዳንዶች የሚሰሩት ሥራ ጊዜያዊ ሰላምንና ጥቅማ ጥቅምን የሚያስገኝ በመሆኑ ብልጠት እንጂ ባርነት እንዳልሆነ አድርገው ያስቡ ይሆናል።

ባርነት መገለጫው ብዙ ነው። ባርነት የአንድ ግለሰብ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ተገርስሶ በሌላ ግለሰብ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠረው ማለት ነው። ባሪያ ሰው ይምሰል እንጂ የተፈጠረለትን ዓላማ ከመፈጸም አኳያ ግን ከቤት እንስሳ አይለይም። ይነሳል፣ ይሰራል፣ ይበላል፣ ይተኛል። የራሱ ዓላማ የለውም። ዓላማ እንኳን ቢኖረው ድብደባን ወይም ሞትን ፈርቶ ለሌላ ሰው ፈቃድ ይገዛል፤ በዱላም ይነዳል። ባርነት የቁም ሞት ነው።

ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ሰው መግደል ኢ-ፍትሃዊ ነው ብሎ የሚያምን ግለሰብ ንፁሃን  በወያኔ አጋዚ ጦር እንደ እንስሳ እየታደኑ በተገደሉባት ኢትዮጵያ ውስጥ ዝም ብሎ መኖርን ከመረጠ የራሱን እውነት ረግጦ ሌሎች በላዩ እንዲሰለጥኑ ፈቅዷልና ይህ ሰው ባሪያ ነው። ነፃ ሰው ያለፍርሃት ለእውነት የሚቆም ነው። እውነት ደግሞ እውነት የሚሆነው ጊዜና ሁኔታዎች ሲመቻቹ ብቻ አይደለም። እውነት ሁልጊዜም እውነት ነው፤ ሁልጊዜም ሊነገር ይገባዋል። የአንድ ሰው የመኖር ዓላማ እየዋሸም፣ ማንነቱን እየካደም ዝም ብሎ የመተንፈሻ ጊዜውን ማራዘም ብቻ ከሆነ በእውነት ያ ሰው ከቤት እንስሳት እንዴት እንደሚለይ እራሱን ሊጠይቅ ይገባዋል። "ባሪያም ሆኜ ህይወቴን ባተርፍስ?" የሚል ካለ ባርነቴን ተቀብሏልና ከነፃ ሰዎች እኩል ክብር ስጡኝ ማለት አይቻለውም!

ጀኔራል ተፈራ ማሞና ጓደኞቻቸው የባርነታቸውን ሰንሰለት ሰብረው ወጥተው ነፃነት በማይወድ ሥርዓት ፊት ነፃነታቸውን አስመስክረዋል። ወያኔና አሻንጉሊት ዳኞቹ እነዚህን ዜጎች ለሞት ቅጣት እና ለእድሜ ልክ እስራት ዳርገዋቸዋል። ነገር ግን መንፈሳቸውን ሊገዙት ወይም ሊገድሉት አይችሉም። የነፃነት መንፈስ እነሱ በሚሳለቁበት ፍርድ ቤት እና ወያኔ ባሰለፈው ጦር ጉልበት ሊታሰር አይችልም። ይህ የነፃነት መንፈስ ደግሞ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ጥማት ነው።

የሚሊዮኖች የነፃነት ጥማት 38 ጀግኖችን በማሰር እና በመግደል ሊገታ አይቻልም። ሚሊዮኖች በእነሱ መስዋዕትነት ይነቃቃሉ። በነፃነት የመመራመር መብቴ ይከበርልኝ ከሚለው የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ጀምሮ በሰላም ልረስ እስከሚለው ገበሬ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃነት ጥማት ክፉኛ ተጠቅቷል። ወታደሩን ዘረኝነት አንገፍግፎታል። መንግሥት ሰራተኛው አድሎ መሮታል። በአገዛዙ ግዴለሽ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እና ዘረፋ ምክንያት ለረሃብ፣ ለዋጋ ንረት፣ ለሥራ አጥነት እና ለበሽታ የተዳረገው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዜጋ የአመራር አማራጭ ጠምቶታል፤ ከአገሪቱና ከሕዝቧ የተመዘበረው ገንዘብ እንዲመለስ እና ሌቦቹ ለፍርድ እንዲቀርቡም ናፍቋል። ከእነዚህ ጉድለቶች እና ስጋቶች ባሻገርም የሃገራቸው ህልውና የሚያሳስባቸው በዝተዋል። በእንዲህ አይነት ቅራኔ ላይ የተመሰረተን የሕዝብ ተቃውሞ ማቆም አይቻልም። ጥቂቶችን በመግደል የአንድ ሕዝብ ቅራኔ ሊጠፋ አይችልም። የሕዝብን የነፃነት ጥም ፈጽሞ ለማጥፋት ሕዝቡን ጨርሶ  ማጥፋት ይሻል፤ ያ ደግሞ የማይቻል ጉዳይ ነው።

ይህንን ለማወቅ የአገዛዙ ቁንጮዎች ብዙም መመራመር አያስፈልጋቸውም። በዓለም ታሪክ ውስጥ ስለወደቁ አምባገነኖች አንዲት መጽሃፍ እንኳ ማንበብ በቂ ነበር። ነገር ግን አምባገነኖች ከታሪክ ይማራሉ ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው። መለስ ዜናዊ የሚፈልገው እስከቻለው ድረስ በመግደል፣ በማሰር እና በማሳደድ የስልጣን እድሜውን ማራዘም እና እራሱን ፍርድ ፊት ከመቅረብ ማትረፍ ነው። ለዚህም እሱ መሥራት እንዳለበት የሚሰማውን እየሠራ ነው።

እኛስ ምን እያደረግን ነው? መሥራት የሚገቡንን ጉዳዮችን እየሠራን ነው? እስከ መቼ ነው የወያኔ ገደብ-የለሽ ግፍ በሕዝባችን ላይ መውረዱን እንዲቀጥል የምንፈቅደው? ያስሩናል፤ ይገድሉናል፤ ያሳድዱናል፤ ይዘርፉናል፤ ይሳለቁብናል፤ መርጠን ባልተወለድንበት ዘር ምክንያት ይተፉብናል፤ በአያቶቻችን ደም የተለወሰውን አፈራችችንን፣ ምድራችንን ለባእዳን ይሸጡብናል፤ ልጆቻችንን እርስት ያሳጡብናል፤ እንዳሻቸው ያደርጉናል። እንደሚወድቁ አስቀድመን ተናግረናል። እኛ የምንታገለው ትግል አሸናፊው ቀድሞ የታወቀለት ነው። እውነት ሁልጊዜም ስለሚያሸንፍ፤ እኛ ደግሞ እውነትን ስላለን ዛሬም ይሆን ነገ ወይም ከነገ በስቲያ ማሸነፋችን አይቀርም። ነገር ግን ይህን ትግል እኛ መቋጨት ስንችል ወደ ቀጣዩ ትውልድ መሻገር አለበትን?

ጥቂቶች ተነስተዋል። "ግደሉን፣ እሰሩን፣ ንብረታችንን ውረሱ፤ ዘረኛነት እና አምባገነንነት ከምድራችን እስኪጠፉ አምፀናል፤ እቤት አንገባም!" ብለዋቸዋል። የተቀረነውስ የት ነው ያለነው? የዘመናችን በላይ ዘለቀዎች፣ የእናት አገር ታዳጊዎች የት ናቸው? የተቀረነውስ ነፃ ሰዎች ከወዴት ነን?

ዛሬ የጠኔ፣ የረሃብና የስደት ምሳሌዎች ሆነናል። በዘመናቸው የመጣውን እክል በጀግነነት ተጋፍጠው ነፃ አገር ትተውልን የሄዱት አባቶቻችን የዛሬውን ጉዳችንን የሚያዩ ከሆነ በየመቃብሮቻቸው ውስጥ መገላበጣቸው አይቀርም። ሕይወት እንደ ዱላ ቅብብሎሽ ውድድር ነች፤ ቀድሞ የሮጠው ቀጥሎ ላለው ሯጭ ሊሮጥለት አይችልም፤ ቀጣዩ መስመር ላይ ያለው ሯጭም ወደ ኋላ መጥቶ ዱላውን መቀበል አይችልም! አባቶቻችን በጀግንነት ሩጫቸውን ሮጠው ዱላውን አቀብለውናል። ልጆቻችን ደግሞ እኛ የራሳችንን ሩጫ በጊዜ እንድሮጥላቸው ይፈልጋሉ፤ አለበለዚያ እዳው ለእሱ ያድራል። የት አለን? የትስ ደርሰናል? የትውልዳችን ቁም ነገሩ ምንድን ነው?

## ለነጻነታችንና ለተዋረደው ስብዕናችን መከበር ስንል ልንከፍለው የማንፈልገው መስዋዕትነት እንደሌለ ወያኔን የማሳወቂያ  ጊዜው አሁን ነው ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ይጠብቅሀል እያለህ ነው። ይህ ስድብ ነው። ይህ ታሪክን ማንቋሸሽ ነው። ይህ ከታሪክ ለመማር አለመቻልን የሚያሳይ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ሞትና እስራትን ከነጻነት በላይ አድረጎ የሚመለከት ቢሆን ኖሮ፣ አገራችን ዛሬም ድረስ በጣሊያን አገዛዝ ስር በወደቀች ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ በሞትና በእስራት ነጻነቱን አሳልፎ የማይሰጥ መሆኑን ለማሳየት ታሪክ እንጥቀስ ብንል ወረቀቱም አይበቃንም። ይህን የአገራችን ህዝብ ያውቀዋል፤ ወያን ግን ገና ያወቀው አይመስልም።

### ውድ ኢትዮጵያ ህዝብ፣

ወያኔ ዝምታን እንደፍርሀት በመቁጠር መያዢያ መጨበጫ ያጣ እርምጃ በመውሰድ ላይ ነው። ዛሬ በግንቦት 7 አባላትና በወታደራዊ መኮንኖች ላይ የተላለፈው ውሳኔ አለማቀፍ ትኩረት ይሳብ እንጅ፣ አንተ ባልታወቀ ና ባልተነገረ ፍርድ የሞትና የእድሜ ልክ እስራት ፍርደኛ መሆንክህን ጠንቅቀህ ታውቃለህ። ዛሬ ይህ ዝምታህ ማብቃት እንዳለበት ልናስታውስህ እንወዳለን። ወያኔን እንደማትፈልገው በግንቦት 1997 ምርጫ ወቀት በግልጽ ተናግረሀል። ከዚያ በሁዋላ የምትወስዳቸው እርምጃዎችም ይህን እውነታ የሚያጠናክር ነው። ዛሬ ከአንተ ጋር እጅና ጓንት በመሆን ይህን የአውሬዎች አገዛዝ የምናስወግድበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። ስለዚህም አስተዋፅኦህ በሁለም መስክ ይፈለጋል። መደገፍ ያለባቸውን ታጋዮች ደግፍ፣ ለወያኔው አገዛዝ  ግብር አትክፈል፣ በቡድን እየተደራጀህ የወያኔ ሰላዮች ከሚያደርሱብህ ተጽኖ ተከላከል። አጋጣሚዎች ሲመቻቹልህም በተለያዩ አካባቢዎች የፈጠርካቸውን ድርጅቶች በአንድ ላይ በማቀናጀት በወያኔ ላይ ያለህን ተቃውሞ አስነሳ። እንደአካባቢህ ተጨባጭ ሁኔታ እያየህ የወያኔ አገዛዝ  ተመቻችቶ እንዳይገዛ የሚያደርጉ እርምጃዎችን ውሰድ። ለነጻነታቸው ሲሉ በእስር ላይ የሚገኙ የነጻነት ታጋዮችንና ቤተሰቦቻቸውንም በሞራል፣ በገንዘብና በምትችለው ነገር ሁሉ እርዳቸው። ወያኔ ለነጻነት የሚደረገውን ትግል ከሚያኮለሽበት መንገድ አንዱ፣ የነጻነት ተጋዮችን ቤተሰቦች ማሰቃየት ነው። ይህን ተረድተህ የነጻነት ታጋዮችን ቤተሰቦች ለመደገፍ ወደ ሁዋላ አትበል።

ለነጻነት የሚደረገው ጉዞ ረጅምና ፈታኝ ሊሆን ይችላል፤ ነጻነትን የሚሹ ግን ሁሌም በአሸናፊነት እንደሚወጡ ታሪክ ምስክር ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

# አሰቂኙ የወያኔው ፍርድ ቤት ውሳኔና የግንቦት 7 አመራር አባላት

**ውድ አንባቢያን፣ የወያኔው አስቂኝ ፍርድ ቤት በግንቦት 7 አመራር አባላትና በሌሎችም የጦር መኮንኖች ላይ የሰጠውን ብይን አስመልክቶ ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፤ ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌና ከአቶ መስፍን አማን ጋር የተደረገውን ቃለ ምልልስ እንድታነቡት እንጋብዛለን**

**ጥያቄ፤** እንደሰማችሁት የወያኔ የይስሙላ ፍ/ቤት ዛሬ ታህሳስ 13ቀን 2002 በተወሰኑ የግንቦት 7 አባላትና በወታደራዊ መኮንኖች ላይ የሞትና የእድሜ ልክ ውሳኔ አስተላልፏል። ሞት ከተፈረደባቸው 5 ሰዎች መሃል ስለሆናችሁ ለመሆኑ ምን ትሰማችሁ? ከዶ/ር ብርሃኑ ልጀምር

**ዶ/ር ብርሃኑ፤** አመሰግናለሁ። በእንዲህ አይነት ነገር እኮ ምን ተሰማህ ብሎ መጠየቅ ችግር ነው የማትጠብቀው ሲሆን፤ እላይ እታች አይቶ የሚወስን ፍርድ ቤት ሲኖር፤ ማስረጃ ቆጥሮ ማስረጃው ተቀባይነት አለው የለውም ብሎ መዝኖ ፍርድ የሚሰጥ ዳኛ ቢኖር ልትል ትችላህ። ይሄ እኮ መለስና በረከት ቁጭ ብለው በማን ላይ ምን እንወስን ብለው በዚህ ድቃቂ እናገኘዋለን ብልው ከሚገምቱት የፖለቲካ ጥቅም ጋር መዝነው የምግፋት ነገር ነው ስለሆንም ምንም የሚገርም ነገር አይደለም። የምትጠብቀው ነው አንድ ነገር ግን በጣም ከዚህ ውሳኔ ጋር ግልጽ እየሆነ የመጣው በዚህ ትግል ውስጥ ምን ያህል እንደተሸበሩ፤ የዚህ የግንቦት 7 እንቅስቃሴ እንቅልፍ እይነሳቸው እንደሆነ በርግጥ እነሱን ከዛ ከተቀመጡበት ያሳፋሪና ዘግናኝ አምባገነንነት ሊያነሳ የሚችል የህዝብ ትግል ሊቀሰቅስ የሚችል እንቅስቃሴ የትኛው እንደሆነ በደንብ በግልጽ ተረድተው ለሌላውም ያሳወቁበት ጊዜ ይመስለኛል።

**ጥያቄ፤** አቶ አንዳርጋቸውስ በዚህ ላይ የሚጨምሩት ነገር አለ?

**አቶ አንዳርጋቸው፤** ምን ተሰማህ ለሚለው ምንም የተሰማኝ ነገር የለም። ባጭሩ ከዚህ በላይ ምንም መናገር የሚቻልበት ጉዳይ አይደለም። ያልጠበቅነው ጉዳይ ቢሆን ነበር ብዙ መናገር የሚቻለው የተጠበቀ ነው እንደተባለው ከእንዲህ አይነት ወራዳ ፍርድ ቤት ምንም ሊጠበቅ አይችልም፡ የመለስን ትእዛዝ ነው የሚያስፈጽመው እንጂ በህሊናቸው ተጠቅመው የሚዳኙበት ፍርድ ቤት ስላልሆነ ከሞት በላይ ሌላ ፍርድ መለስ ወስኑ ቢላቸው የሌለን ነገር ለመወሰን ወድ ኋላ የማይሉ ዳኞች ስለሆኑ ምንም አልተገርምኩም

**ጥያቄ፤** አቶ መስፍንስ የሚያክሉት ነገር አለ?

**አቶ መስፍን፤** የተለየ የማክለው ነገር የለም። ያው ገና ክሱን ሲጀምሩት ጀምሮ የዚህ አይነት ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚችሉ እገምት ነበር። የተለየ ምንም የፈጠረብኝ ነገር የለም ግን ያው አሁን ባለው ሁኔታ ወያኔ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳለና ፍርሃት ውስጥ ሆኖ የሚያረገውን ያጣበት ሁኔታ ውስጥ እንዳለ የሚያሳይ ስለሆነ ያ ብቻ ነው የሚገርመኝ በግሌ ምንም የፈጠረብኝ ነገር የለም።

**ጥያቄ፤** ዶ/ር ብርሃኑ በመጀመሪያው ላይ ለመጥቀስ ሞክረዋል። ወያኔ ይሄን ውሳኔ ሲወስን ምንምን ነገሮችን ግምት ውስጥ አስገብቶ እንደሆነ መገመት ይቻላል? ባጠቃላይ በግንቦት 7 ንቅናቄ ከመደናገጥ ና መሸበር ውጭ ሌሎች ምክንያቶችን ማሰብ ይቻላል? ምናልባት ያልተነሱ ነገሮች ካሉ በዚህ ላይ ብታክሉበት

**ዶ/ር ብርሃኑ፤** እሱማ ዋናው እኛ ላይ የሚፈረደው ፍርድ ዋናው መልክት አገር ውስጥ እና ከዚያም ውጭ ላለው ህዝብ ማስፈራሪያ ነው። ይህ መንግስት ካሁን በኋላ በህዝብ ተቀባይነት አግኝቼ ህዝብ የሚለውን ሰምቶ ደግፎ ከስልጣን ያቆየኛል የሚለውን ተስፋውን ከምርጫ 97 በኋላ አሟጦ የጨረሰ መንግስት ነው። ይሄ መንግስት የያዘውን የዘረኝነት አካሄድ፤ የያዘውን የብዝበዛ አካሄድ፤ የያዘውን አገር የመሸጥ አካሄድ፤ የያዘውን አገር የማዋረድ አካሄድ፤ ሊቀጥልበት የሚችለው በጉልበት ሰውን አስፈራርቶ ቅስሙን ሰብሮ በፍጹም "እኔን መቃወም ማለት በእሳት መጫወት " ነው ብሎ እንዲያምን በማድረግ ብቻ ነው ብሎ የሚያምን ነው። ይሄ ህዝብ አንዴ አንገቱን ቀና ያረገ ቀን አንዴ የመጣ ነገር ይምጣ ብሎ የታገለ ቀን በጥቂት ቀናት ሊያፈራርሰው የሚችል የእምቧይ ካብ የሆነ መንግስት እንደሆነ ያውቀዋል ስለዚህ እስከሚችለው ድረስ አስፈራርቶ እስከሚችል ድረስ አሸማቆ የፍርሃት ማህበረሰብ ፈጥሮ መኖር ነው የሚፈልገው። ሞት ፍርድ ፈርጃለሁ ሲል እኛ ላይ፤ ሌላው ይንቀጠቀጣል ፤ ሌላው ሰው ይርበደበዳል ሌላው ሰው አንገቱን ቀና አያደርግም የሚል ስሌት ነው ያለው ይህን ስሌቱን ደግሞ ገና ክስ ሲመሰርት በከሰሰው ልክ የሚፈርድለት ፍርድ ቤት አለው። በዛ በኩል ነው ያደረገው። መሄጃ የለህም ነው መለዕክቱ። ፍርድ ቤት ብትሄድ እኔው ነኝ፡ ፖሊስ ጋር ብትሄድ እኔው ነኝ የትም ብትሄድ እኔው ነኝ ያለሁት መነቃነቂያ ስለሌለህ አርፈህ ተገዛ ለማለት ነው ህብረተሰቡን የሚፈልገው ።ባለፈው መለስ የተናገርው ትዝ ይለኛል"**በሩ ሲዘጋብህ ግድግዳ በጥሰህ ትወጣለህ"** ያለው ነገር አለ የኢትዮጵያን ህዝብ በሩን ሁሉ ዘግተውበታል ነጻነቱን ለማግኘት ግድግዳ መበጠስ ያለው አማራጭ እሱ ብቻ እንደሆነ እየነገሩት ነው ያለው።

**ጥያቄ፤** አቶ አንዳርጋቸው ጉዳዩ ከሚመጣው ምርጫ ጋር የሚያያዝበት ጉዳይ አለ?

**አቶ አንዳርጋቸው፤** በምርጫው ላይ ምንም አይነት ተጽኖ ያመጣል የሚል እምነት የለኝም። ምርጫ የሚባለውን ቃል ለመጠቀም የሚከብደኝ ስለሆነ ነው። የራሱ የወያኔ አጀንዳ ነው ምርጫ። ከምርጫ ጋር የተያያዘ ነው ብሎ ማለቱ ግን የሚከብድ ነው ። ብርሃኑ በተናገረው ላይ መጨመር ያለበት ነገር፤ የነመለስ ጥፋት እንደ ማናቸውም አምባገነኖች ጥፋት ሰዎችን ለተለያየ ተቃውሞና አመጽ የሚቀሰቅሰው ሁኔታ በሃገር ውስጥ እያለ፣ የሚያምጹትን ሃይሎች በማሰር በመግደል በማሳደድ ችግሩን እንፈታለን ብለው ማሰባቸው ነው ። የጀኔራሎቹ ባመጽ እንቅስቃሴ ተሳትፈዋል አልተሳተፉም፤ ግንቦት 7 እነሱን ረድቷል አልረዳም አይደለም ዋና መሰረታዊ ጥያቄ ፣ በሃገሪቱ ውስጥ ያለው ችግር ጀነራሎቹም አስቀድሞ ከስር በፊት በተለያዩ አደባባዮች የተናገሩት፣ የአገር ቤቱንም ህዝብ በውጭ የሚገኘውንም ህዝብ እያቆሰለ ያለው፣ ኢትዮጵያ የ80 ሚልዮን ህዝብ አገር መሆኗ ቀርቶ ጥቂት ዘረኞች ወታደራዊ የስለላ መዋቅሩንና ትልልቁን የቢሮክራሲ መዋቅር ከዛ በኋላ ደግሞ ጥቅላላ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ተቆጣጥረው ሌላውን ዜጋ ግማሹን በሁለተኛ ሌላውን በሶስተኛ ዜግነት ደርጃ እያዋርዱ እየቀጠቀጡ ለመኖር ቆርጠው የተነሱበት ሁኔታ ነው፤ ያ አንግፍግፏቸው ያ መሯቸው ነው እነዚህ ሰወች የተነሱት እና ያ ሁኔታ በማሰር በማስፈራራት በመግደል ሊጠፋ የማይችል ሁኔታ ነው። ይህ ሁኔታ መለስና ጓደኞቹም ውሎ አድሮ ከዚህ ቀደም እንዳየናቸው በሌሎችም አለማትም ሆነ ባገራችን አምባገነኖች የታሪክ ቆሻሻ መከመሪያ ቦታ ወስዶ የሚያስቀምጣቸው ሁኔታ ነው ያለው። የሳቱት ነገር እነመለስ ለፍርድ ቤቱ እንዲዎስኑ ብለው ትእዛዝ ሲሰጡ ፤ ፍርድ ቤቱም ይሄን ትዛዝ ሲያስፈጽም የረሳው ነገር ይሄ ነው። በደል ባለበት፤ ጭቆና ባለበትና ዘረፋ ባለበት ቦታ ላይ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ባስተዳደራዊ ውሳኔ ወይም በወታደራዊ እርምጃ ይሀን የህዝብ ትግል አፍኖ ማቆየት አይቻልም። ይህንን ነው በዛሬው ቀን ማስተላለፍ ያለብን ፤ የኢትዮጵያ ህዝብም የሚያውቀው ይመስለኛል።

**ጥያቄ፤** አቶ መስፍን ይሄ ነገር በግንቦት 7 እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረው አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ተጽእኖ ይኖራል ወይ?

**አቶ መስፍን፤** ይህም ውሳኔ ሆነ ሌሎች የወያኔ እርምጃዎች ግንቦት 7 ህዝብን አንቀሳቅሶ ይህን ስር አት ለመገርሰስ በሚያደርገው ጥረት ላይ ቅንጣት ታህል ተጽኖ አያሳድርም ብዬ ነው የማምነው። ይህ አይነት ነገር እዛው የፍርድቤት ውሳኔ ነው ሆኖ የሚቀረው እንጂ በግንቦት 7 እንቅስቃሴ ለይ በግንቦት 7 የትግል ሂደት ላይ ፣አንዳችም ተጽኖ የሚያሳድር ነገር የለውም። በሞራልም በመነሳሳትም በሌሎችም ነግሮች ላይ እነሱ እንዳሰቡት ወይም እንደፈለጉት ሳይሆን እንዲያውም በግንቦት 7 ውስጥ ያለውን ለዚህ አላማ ለዚህ ትግል የመነሳሳቱን ሁኔታ የበለጠ የሚጨምረው ሆኖ ነው የሚታየኝ። በዋነኝነት ከዚህ ቀደም የተናገሩት ዶ/ር ብርሃኑም ሆኑ አቶ አንዳርጋቸው እንደገለጹት ወያኔ ከሁሉም አምባገነኖች የተለየ የሚያደርገው ከብዙ ታሪኮች የመማር ችሎታ በጣም አነስተኛ መሆኑ ነው፤ ከዚህ ቀደም የነበሩ አፋኝ ስርአቶች አፈናቸውን በማጠናከር ወይንም ሰዎችን በማጥቃት የህዝብን መነሳሳት መግታት የሚችሉ ይመስላቸው ነበር፣ ግን ያነገር መቼም ተሳክቶ አያውቅም። የዛሬውም ውሳኔ ወሳኞቹንም ሆነ ውሳኔው እንዲተላለፍ ትዛዝ ያስተላለፉን ባለስልጣናት የፈልጉትን አይነት ውጤት አያስገኝም በኛ እንቅስቃሴ ላይም ቀደም ብየ እንዳልኩት ቅንጣት ታክል ተጽኖ አያስከትልም።

**ጥያቄ፤** ጥሩ ወደ መጨረሻ ጥያቄ እየሄድኩ ነው በእስር ቤት ውስጥ ለሚግኙትም በአጠቃላይም ለኢትዮጵያ ህዝብ የምታስተላልፉት መልእክት አለ? ዶ/ር ብርሃኑ ሊጀምሩ ይችላሉ።

**(ወደ ገጥጽ 4 ዞሯል)**

## ወያኔን ከነተከለብን ዘረኝነት ማስወገድ

. . . ከገጽ 1 የዞረ

የወታደራዊ ጉዳይ የሳሞራ የኑስ ግዛት ሲሆን የፍትህ ተቋሙን የመቆጣጠር ሥራ የመንበረፀሃይ ታደሰ ኃላፊነት ነው። በዚህ አሳሳችና ዘረኛ አወቃቀር የመንግሥት ሥልጣን ስማቸው ከላይ በተዘረዘሩ ሰባት ሰዎች መዳፍ ውስጥ የገባ መሆኑ **እውነት** ነው። ሰባቱም ሰዎች የአንድ አካባቢ ተወላጆችና ወያኔዎች መሆናቸው ደግም ሌላው የፈጠጠ **ሃቅ** ነው።

ይህን ዓይን ያወጣ ዘረኛ አደረጃጀት አምባሳደር ዳግላስ ግራፍትስ አቅልለው "ለኢትዮጵያ አይበጅም" ይበሉት እንጂ ጉዳቱ ከዚያ በጣም የላቀ ነው። ይህ መዋቅራዊ ዘረኝነት ሕልውናችንን የተፈታተነ ጉዳይ ነው። ይህ ችግር ከእኛም አልፎ ወደ ሌሎች አገሮችም በቀላሉ ሊዛመት የሚችል ክፉ ደዌ ነው።

በዚህም ምክንያት ወያኔን ከነተከለብን ዘረኝነት ማስወገድ ከችግሮቻችን ሁሉ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር በመሆኑ በኅብረት እንነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## አሰቂኙ የወያኔው ፍርድ ቤት

. . . ከገጽ 3 የቀጠለ

**ዶ/ር ብርሃኑ** በመጀመሪያ መስፍን ቅድም ባነሳው እና አንተ አንስተህ መስፍን ወደ መለሰው ጉዳይ እንመለስ፣ እንደ ግንቦት ሰባት አይነት ድርጅት በእለት ተለት በሚፈጠሩ ትናንሽ ነገሮች ላይ ተመስርቶ ውሳኔ አይወስንም፤ ወደፊት እንዴት ነው የምንሄደው የሚለውን ነገር ቀድሞ አስቦ የሚያዋጣውን የህዝቡን ትግል ወደፊት የሚወስደው የትኛው ነው ብሎ ቀይሶ ያን የቀየሰውን መንገድ ይዞ ይሄዳል እንጂ ዛሬ የወያኔ መንግስት ይህን አደርገ ነገ ያን አደረገ ብሎ በየጊዜው የሚቀየር አይደለም። የእለት ተቀን አንቅስቃሴው በአንዲህ አይነት ነገሮች የሚወሰን አይደለም። ግንቦት 7 ምንም ከፍም ዝቅም የሚያደርገው የለም። አጥንቶ አስቦ የሚያዋጣውን መንገድ የትኛው ነው ብሎ ተዘጋጅቶ የሚያድርግ ስለሆነ አሁንም የወያኔን ምንነት በሚመለከት የመለስና የበረከት ሁናቴ በሚመለከት ምንም የሚጨምርው ነገር የለም ከዚህ በፊት ሲያደርጉት የነበረ ነው ወደ ፊትም ያደርጉታል። የሚፈራ ሰው እስካገኙ ድረስ ለማስፈራራት አይመለሱም። ከዛ በኋላ ላነሳኸው ጥያቄ ግን በእነርሱ እጅ ላይ ሆነው በእስር የሚማቅቁ በአጠቃላይ ማለት የሚቻለው አይዞአችሁ በርቱ የነፃነት ቀን መምጣቱ አይቀርም፤ በእንዲህ አይነት ምንም መሰረት በሌለው ፍርድ ውሳኔ ቅንጣት ታክል ሊበግራችሁ አይገባም። በአገራችን ውስጥ ያለው በደል ሞልቶ ፈሷል ይህን በደል የማስቆም ግዴታ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው፤ እነዚህን ሰዎች ዝም ብለን ካየን ግለሰቦችን ሳይሆን አገር ለማጥፋት የማይመለሱ መሆናቸው ነው። ዘረኞች ናቸው። ነውረኞች ናቸው። የሀገር ስም የሚያጠፉ ሰዎች ናቸው። ዝም ብለን ልንመለከታቸው፤ ዝም ብለን ልናያችው በፍጹም አይገባም፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እነዚህን ሰዎች በሀገሪቱ እና በህዝባችን ላይ ከፈጠሩት አበሳ ለማላቀቅ የዜግነት ግዴታውን በተለያየ መልክ መወጣት ያለበት ጊዜ ነው። አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ እኔን አይመለከተኝም ብሎ ካዳር ቆሞ የሚመለከቱበት አይደለም። ማርቲን ሉትር ኪንግ እንዳለው በእንዲህ አይነት የአበሳ ጊዜ ወራዶች የሚያደርጉትን ነገር ሳይሆን ውርደትና እንዲህ አይነት ግፍ ሲካሄድ ዝም ብሎ ያየውን ነው እና ታሪክ የሚመዘግበው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአሁኑ ጊዜ ዝም ብሎ ከዳር ቆሞ የሚያይው ነገር እንደሌለ እና በዚህ ትግል ውስጥ በሚችለው ነገር ውስጥ ገብቶ ይህንን የአበሳ ግዜ ማሳጠር እንዳለብት ነው ማሳሰብ የምፈልግው።

**አቶ አንዳርጋቸው** በኔ በኩል ህዝቡ የሚኖረው ኑሮ ስለሆነ ሁሉንም ነገር ስለሚያውቀው ይህንን ሥርዓት ለማስወገድ ምን ማድረግ እንዳለበት ከውጭ መነገር ያለበት አይደለም። ነገር ግን በእኛ በኩል ዛሬ የሆነው ነገር ቅድም አቶ መስፍን እንዳለው ለመታገል ያለንን ቁርጠኝነት መስዋእት ለመክፈል ያለንን ዝግጁነት የበለጠ የሚያጠናክር ነው የሚሆነው። በዚህ ፍርድ ቤት ውስጥ መረሳት የሌለበት እድሜ ልክ ከፈረደባቸው ሰዎች መካከል አንዱ እድሜው በማለቅ ላይ ያለው የ 83 አመት ሽማግሌ የራሴው አባት ያለበት ነው። ወያኔን የሚያንገፈግፈው ነገር ሰው ሲገርፉ ስትገርፉ ነበር ብሎ በአደባባይ የተገረፉትን ሰዎች በተመለከተ ምስክርነት መስጠት የሚችል በወያኔ ዘበኛ ፊት በመናገር በቁርጠኝነት በሚያሳየው ድፍረት ነው እያንገበገበው ያለው። እንደዚህ አይነት መስዋትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆኑ በጣም በርካታ የሆኑ ሰዎች ያሉበት ሀገር ነው። ግንቦት 7 ደግሞ **ይቀጥላል**

በሁሉም መስኩ እነዚህን ዜጎች ለመታደግ መደረግ ያለበትን ሁሉ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። የማድርግም አቅም መፍጠር የሚችል ነው። እንደሚባለውም ታሪክ መለስ እና መለስን ከመሳሰሉ አምባገነኖች ጎን ሳይሆን የሀገሪቷ ህዝብ በሙሉ በሰላም በእኩልነት መብቱ ተጠብቆና ተከብሮ ከዚህ እጅግ አዋራጅ ከሆን የድህነት ህይወት ውስጥ የሚወጣበትን ሁኔታ ለመቀየር ከሚታገሉ ህይሎች ጎን ነውና ለህዝብ መናገርና ማስተላለፍ የምፍልገው መልእክት እጅግ በከረረ መልኩ ትግላችን የሚቀጥልበት ሁኔታ እንደሚመጣ እንዲያውቀው ነው።

**ጥያቄ፤** በእርሶ ላይ ከተሰጠው ውሳኔ በተጨማሪ በአባትዎም ላይ ውሳኔ ተላለፉዋል ፤ ከጤናቸው አንፃር ውሳኔው ከባድ ነው፣ ይህ ምን ስሜት ፈጠረብዎ?

**አቶ አንዳርጋቸው** እኔ እያየሁት ያለሁት ሁሉንም ነገር ሀገርና ወገን ካለበት ጭንቅና አሳር አኳያ ነው። ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ተመሳሰይ በሆነ መንገድ እጅግ አስፈሪና አስከፊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሀገሪቷም ህዝቧም ወድቁዋል። እኔ የእርሱ አባቶች የከፈሉትን የአርበኝነት መስዋትነት አውቃለሁ። አሁን ሀገሪቷ ከውጭ ወራሪ ባልተናነሰ መንገድ የእኛው ቋንቋና መልክ ባላቸው ሰዎች ወድቃለች፤ ሀገሪቱ እጅግ በከፋ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለችው። ስለዚህም ይህን አይነት ሁኔታ ለመቀየር አንዳንዱ በልጆቹ ሌላው በአባትና በእናቱ በኩል ሌላውም በራሱ መስዋእትነት ለመክፈል የሚገደድበት ሁኔታ ነው ያለው። ከእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ማምለጥ አይቻልም። ይህ ማለት በግዴለሽነት አንድ ሰው አባቱን ወይም ልጁን ባላመውደድ የሚናገርበት ሁነቴ አይደለም። ያለንበትን እጅግ አስፈሪና አሳፋሪ ሁኔታ ለተመለከተ ከእንዲህ አይነቱ ግለሰባዊ ስሜት በላይ ተሻግረን ሄደን ስራዎቻችን በሙሉ ልብና በቁርጠኝነት ለመታገል ከመንቀሳቀስ ውጭ ምንም አማራጭ የሚተውልን አይደለም የሚያሳዝን ነገር ነው። ነገር ግን አዝነን እየቆዘምን ከምንሰራው ስራ ወደ ኋላ ሊያደርግን የሚገባ ነገር እንዳልሆነ ነው የማምነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ መረሳት የሌለበት ደጋግሜ ተናግሬዋለው በአንድ አጋጣሚ የኔ አባት ስለሆነ በሬድዮ ፕሮግራም ስሙ ሊነስ ይችላል፤ ግን በተመሳሳይ እድሜ በጣም በርካታ ሰዎች ግማሾቹ በእስር ቤት ሌሎቹ ደግሞ ሀገሪቷ እራሷ ትልቅ እስር ቤት ሆናባቸው መከራቸውን የሚያዩባት ሀገር መሆኑ ግምት ውስጥ መግባት አለበት። አባቴን ወይንም የሌላውን አባት በማሰር፣ ልጁን በማሰር ወይንም በመግደል አንድ ሰው ለነፃነትና ለሙብት መከበር የሀገሩን ክብርና የወገኑን ክብር ለማስጠበቅ የሚያካሂደውን ትግል አቆማለው የሚል ቅዥት እንዳይኖረው ነው የሚገባው፤ የፈለጋችሁትን መግደል ማሰር ትችላላችሁ ነገር ግን በባርነት አታንበረክኩንም ይሄ ነው መልሳችን መሆን ያለበት።

**አቶ መስፍን፣** መናገር የምችለው እነዚህ ሰዎች ሌላ ምንም ነገር አይደሉም ሀገር አጥፊዎች ናቸው። የነገ ኢትዮጵያን የነገ ተስፋችንን እያጠፉብን ያሉ ሰዎች ናቸው። በተለይ በእኔ እድሜ ለሚገኙ ወጣቶች የማስተላልፍው፣ አገራችንን በግል ጥረንና ሰርተን ልናድግባት የማንችልባት ሀገር እያደረጓት ነው። በተለይ እኛ ወጣቶች የነገውን እድላችንን እና ተስፋችንን ለማለምለም እነዚህን ሰዎች በቻልነው አጋጣሚ በአለን አቅምና ጉልበት እውቀት ታግለን የመጨረሻውን ቀን ለማምጣት እንድንሰራ ነው። ስለዚህ ጥረታችንን አጠናክረን አስትባብረን የነገ ተስፋችንን እንድናለመልም ለኢትዮጵያ ወጣቶች ሁሉ ጥሪየን አስተላልፋለሁ።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org *ወይም* በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661